## ምዕራፍ ፫

መጋቤ፡ኅ/ብ፡ምናሴ፡ወ/ሄ

# ቀመረ አዝማናት

ቤተክርስቲያናችን ይህ ቀረሽ የማትባል ጥንታዊት ታሪካዊት በልማድ አጠራር ብሔራዊት ብቻ ሳትሆን ዓለም አቀፋዊትም ቤተክርስቲያን ናት::

በመሠረቱ ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ያሰኘቻት ወይም በመላው ዓለም እንድትታወቅ ያደረገቻት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስ ቲያናችን መሆኗን የሚያጠራጥር አይሆንም በዚህ አባባል ወይም ሃሣብ አሉታዊ አቋም በመያዝ ደፍሮ የሚከራከር ሰው ይኖራል ብሎ መገመት ፈጽሞ የሚታሰብ አይሆንም::

እንግዲህ ወደ ዋናው መሠረተ ሃሣብ ስንገባ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከማንም ከምንም ያልመጣና ያልተቀላቀለ በዓይነቱና በይዘቱ ከሌላው ዓለም የተለየ የራሷ ፊደል፣ የራሷሥነ ጽሑፍና የራሷ የዘመን አቆጣጠር ያላት ብቸኛዋ አፍሪካዊት ሀገር በመሆኗ ከዓለም የክብር ሰንጠረዥ ገብታ እንድትቆጠር ወይም እንድትመዘገብ አስችሎአታል:: ይህም ክብር ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሣይሆን ለመላው የአፍሪካ ሕዝብ መመኪያ ወይም ኩራት መሆኑ ሁሉም ሠው ሊረዳው ይገባል::

ከላይ እንደተገለፀው ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም ልዩ የሚያደርጋት የራሷ የዘመን አቆጣጠር ስልት ስለአላት ነው::

ይህም የዘመን አቆጣጠር ስልት ረቂቃንና ምጡቃን የሆኑት ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን አባቶችን በኅላና በተለየ መልኩ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከአእምሮአቸው አንቅተው ቅዱሳት መጻሕፍትን አመሳክረው መስፈሪያ መቁጠሪያ ሕግ ሠርተው ጽፈውና ደጉሰው ...ዩልን መጽሐፍ አለ:: መጽሐፉም በፀሐፊው ሥም አቡሻክር



በመባል ይታወቃል :: መጽሐፉ ምንም እንኳ በፀሐፊው ሥም አቡሻክር ተብሎ ቢጠራም መጽሐፉን በማዘጋጀት የተሳተፉት ሊቃውንት ብዙ ናቸው እነሡም:-

- ☞ ሰዒድ ወልደ በጥሪቅ
- ☞ ማኅቡብ መንበጋዊ
- ☞ ዮሐንስ አፈወርቅ
- ☞ ቅዱስ ቄርሎስ
- ☞ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ
- ☞ ዮሐንስ ደማስቆአዊ
- ☞ ማርቆስ ወልደ ቀምበር

ጊዮርጊስ ወልደ አሚድና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን መተ ርጉማንና መምስጥራን ሊቃውንት ይገኙበታል::

እንግዲህ ወደ ዋናው መሠረታዊ ዓላማ ስናመራ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የዘመን አቆጣጠር ስልት በ7 አበይት ክፍሎት ይከፈላሉ::

እነሱም:-

- ዓውደ ዕለት
- ዓውደ ወርሕ
- ዓውደ ዓመት
- ዓውደ አበቅቴ
- ዓወደ ማኅተም
- ዓውደ ቀመር
- ዓውደ ፀሐይ ናቸው፤

7ቱም ዓዕዋዳት የየራሣቸው ትንታኔ አላቸው:: ዓውደ ዕለት ከእሁድ ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ያሉት 7 ዕለታት ናቸው:: እነዚህ አውራጎን ለማግኘት በ7 በ7 ዕለታት ሲመላለሱ ይኖራሉ::

www.ethiopianorthodox.org

ዓውደ ወርህን በጨረቃ አቆጣጠር አንድ ጊዜ 29 አንድ ጊዜ 30 ሲሆን በፀሐይ አቆጣጠር ግን ሁል ጊዜ 30 ነው። ስምን ዓውድ ዓውድ ተባለ ሲባል የዕለት ስብስብ ወይም ድምር ወራቶችን፣ የወራቶች ስብስብ ወይም ድምር ዓመትን ያስገኛልና ዓውድ ተባለ። ዓውድ የሚለው ኃይለ ቃል በነጠላ ሲተረጎም መሰብሰቢያ ማለት ሲሆን ሲሰፋ መገናኛ፣ አደባባይ፣ መቆሚያ፣ መካተቻ ማለት ነው።

- ዓውደ ዓመት በጨረቃ አቆጣጠር 354 ዕለት በፀሐይ አቆጣ ጠር 365 ዕለት ነው።
- ዓውደ አበቅቴ 19 ዓመት ነው። በዚህ ፀሐይና በዑደት የሚገናኙበት ጊዜ ነው።
- ዓውደ ማኅተም 77 ዓመት ነው። ይኼውም ወንጌላዊንና ዓበቅቴን ለማገናኘት የሚረዳ ነው።
- ዓውደ ቀመር 532 ዓመት በዚህ ወንጌላዊ ዕለትና አብቅቴ ይገናኙበታል።
- ዓውደ ፀሐይ 28 ዓመት ነው በዚህም ዕለትና ወንጌላዊ ይገናኙበታል።

ከላይ በቅደም ተከተል የተዘረዘሩትን በአጭሩ ለመረዳት ይቻል ዘንድ ድሜጥሮስ የተባለው ሊቅ ከቅድመ ልደተ ክርስቶስ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ለማወቅ የሚያስችሉ 3 አበይት አቅማር አሉ።

እነሡም፦

- ዓቢይ ቀመር
- ንዑስ ቀመርና
- ማዕከላዊ ናቸው



እነዚህም አበይት አቅማር ሲተነተኑ 12 ይሆናሉ እነሡም ምንና ምን ናቸው ቢሉ፦

- አንቀጽ
- ማኅተም
- መደብ
- መካን
- ዓውደ
- ቀመር
- ገጽ
- ምዕራፍ
- ማዕረግ
- ህላዌ
- ቤትና
- ማኅደር ናቸው።

እንግዲህ ከላይ በተጻፉትና የተገለፁት ኃይለ ቃላት የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር ስልት በዓይነቱም ሆነ በይዘቱ ከምሥራቃውያንና ከምዕራባውያን የተለየ መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው።

የምዕራባውያንና የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር ሰፊ ልዩነት አለ። ይህም የሆነበት ዋና ምክንያት፦

1ኛ. የሄኖክ ሰባኤ አቆጣጠር በ10 ሰባኤ 700 ዓመት 1 እያለ ይቆጥራል። ይህንንም እስከ 10 ቢወስዱት 7 ሺህ ዓመት ይሆናል።

2ኛ. በቀመረ ዳዊት አቆጣጠር 1 መቶውን ዓመት 1 እያለ ይቆጥራል። እስከ 10 ቢወስዱት 1 ሺህ ዓመት ይሆናል።

3ኛ. ሰባኤ ዳንኤል 7ቱን ዓመት 1 እያለ ይቆጥራል። እስከ 10 ቢወስዱት 70 ዓመት ይሆናል።

4ኛ. ሰባኤ ኤርምያ ሰባት ነው። ወደ 10 ቢወስዱት 70 ይሆናል።

5ኛ. ሰባኤ እዝራ 500ውን ዓመት 1 በማለት ነው ወይ 10 ቢወስድ 5000 ይሆናል።

6ኛ. ቀመረ ሙሴ ወይም የኢዮቤልዩ አቆጣጠር መስፈሪያው 25 ዓመት ነው።

7ኛ. ቀመረ ድሜጥሮስ ሲሆን በተለይም የድሜጥሮስ የአቆጣጠር ስልት በዓቢይ ቀመር በማዕከላዊ ቀመርና በንዑስ ቀመር የተከፈለ ሁኖ የረቀቀና የመጠቀ የአቆጣጠር ስልት ነው።

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሱባኤ ሥርዓት 7 ነው 7ም የሆነበት ምክንያት ሰፊና ጥልቅ ሚስጢር አለው።

ይኼውም 7 እንዲሆን ያስፈለገበት ዋና ምክንያት የሰው ልጅ የተፈጠረው ከ4ቱ ባሕርያተ ሥጋና ከ3ቱ ባሕርያተ ነፍስ መፈጠሩን ማለት ስብእ ማለት ከ7 ባሕርያት የተፈጠረ ፍፁም፣ ሕያው ማለት መሆኑን ለመግለጽ ነው፤

አንድም ዲያብሎስ በሥጋ ከይሲ ተሰውሮ አዳምንና ሔዋንን ያሳታቸው በተፈጠሩ በ7 ዓመት መሆኑን ለማስረዳት ነው።

እንግዲህ የምዕራባውያን ወይም የአውሮፓውያንና የኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር ልዩነት የተፈጠረው እንደ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን አባቶች ትምህርት ኢትዮጵያውያኑ ከላይ የተተነተኑትን የአቆጣጠር ስልቶች በዓይነታቸውም ሆነ በይዘታቸው ከአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር መንገድ በእጅጉ የተለየ መሆኑ ነው።

ለማስረዳት ያህል ኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንት የሚጠቀሙበት የአቆጣጠር መንደርደሪያ ወይም መነሻ የሚሆናቸው 44ቱን መናብርተ ክርስቶስ ለማወቅ 24 አጽፈ አወራህ 14 ሠርቀ ሌሊት 6 ሕፀፅ አንድ ሁነው ሲቆጠሩ የአቢይ ቀመርን ጠቅላላ ድምር ይሰጣል። ይኼውም 532 ነው። ይህ ቁጥር ለ4ቱ ወንጌላውያን ሲካፈል 133 ለእያንዳንዳቸው ይደርሳል። ይህም ሰንበተ ማቴዎስ፣ ሰንበተ ማርቆስ፣ ሰንበተ ሉቃስ፣ ሰንበተ ዮሐንስ በመባል ይታወቃል። ሰንበት ማለትም ሱባኤ ማለት ነው ሱባኤም ማለት ፍፀም ምሉዕ ትክክል ማለት ነው።

በዚሁ መሠረት ዓለምን በጥንተ ዮን ለመመርመር በ2 ሺህ 256 ዓመተ ዓለም ግንቦት 26 እሑድ ቀን ማየ አይኅ ዘንሟል በ25 ዓርብ ቀንም ይላሉ በ3 ሺህ 844 ዓመተ ዓለም መጋቢት 23 ረቡዕ ቀን እስራኤላውያን የበጉን መስእዋት በልተው በ24 ሐሙስ ቀን ከግብፅ ወጥተዋል። በ3 ሺህ 845 ዓመተ ዓለም በግንቦት 14 ቅዳሜ ቀን ካሌብና ሰልሞን የተስፋይቱን ምድር አይተው ፍሬ ይዘው ወደ ወገኖቻቸው ተመልሰዋል።



በ4ሺህ 182 ዓመተ ዓለም ሚያዝያ 30 ቀን ማክሰኞ ዕለት ሚጠት ተደርጓል። በ5 ሺህ 42 ዓመተ ዓለም ዳግም የኢየሩሳሌም ምዝባሬ ሆነ በ5 ሺህ 66 ዓመተ ዓለም መስከረም 16 እሁድ ቀን የኢየሩሳሌም ዳግም ሕንፃ ሆነ። ከዳግም ሕንጻ እስከ ልደተ ክርስቶስ 62 ሱባኤ እስከ ስቅለት ቢወስዱት 70 ሱባኤ ይሆናል። በ5 ሺህ 182 ዓመተ ፀሐይ በጥቅምት 4 ቀን ሰኞ እለት እስክንድር ነግሷል። በ5 ሺህ 484 በኅዳር 17 ቀን ሐሙስ እለት አውግስጦስ ነግሶአል። በ5500 ዓመተ ፀሐይ እሑድ መጋቢት 29 ቀን በዘመነ ዮሐንስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተፀንሶአል። በ5 ሺህ 500 ዓመተ ፀሐይ በታኅሣሥ 29 በዘመነ ማቴዎስ ማክሰኞ ቀን ተወልዶአል፡ በ5531 ዓመተ ፀሐይ በጥር 11 በዘመነ ሉቃስ ማክሰኞ ቀን ተጠመቀ፤ በ5534 ዓመተ ፀሐይ በመጋቢት 27 ቀን ዓርብ እለት ተሰቅሎአል ማለትን ከኢትዮጵያውያን በስተቀር ምሥራቃውያኑም ሆነ ምዕራባውያንም ወይም አውሮፓውያን ስለማያውቁት ነው።

ይኼውም በኦሪት ምክንያት ነው። ኦሪት 4 ጊዜ ተጽፋለች።

*1ኛ.በሙሴ ዘመን የተጻፈው ኦሪት ዘሌዋውያን ይባላል።*

*2ኛ.ኦሪት ዘሊቃውንት /የሊቃውንት ኦሪት/ ይባላል።*

ማለት በጥሊሞስ የተባለው የግብፅ ንጉሥ ብዛት ያላቸው የጥበብና የፍልስፍና መጻሕፍትን ካጻፈ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም መልዕክትን ላከ። ይኼውም በእውቀታቸው የረቀቁ፣ በአስተሳሰባቸው የመጠቁ ፀሐፍትንና መጻሕፍተ ነቢያትን ጨምራችሁ ላኩልኝ የሚል ነው። መልእክቱ የደረሳቸው የኢየሩሳሌም ሰዎችም በጊዜው ገናና ንጉሥ ነበረና ሳይወዱ በግዳቸው 72 ፀሐፍት ጨምረው ሲልኩ 2ቱ ከመንገድ ሞቱ። 70ዎቹ ከነመጻሕፍተ ነቢያቱ ግብፅ ከንጉሥ በጥሊሞስ ደረሡ። ከመጻሕፍት ነቢያቱ አንዱ ክፍል የሆነው ኦሪት ዘሌዋውያንን ከእብራይስጥ ቋንቋ ወደ ቅብጥ ቋንቋ መለሱት ወይም ተረጎሙት ይህም ኦሪተ ሊቃውንት ተባለ።

3ኛ. *ኦሪተሳምሪውያን ተብሏል።* ይኼውም ልምናሶር የሚባል የፋርስ ባቢሎን ንጉሥ በእስራኤላውያን ዘምቶ 10ሩን

www.ethiopianorthodox.org

ነገድ ማርኮ በሰማርያ ላይ እጀም የሚባል ሠራዊት ወይም ጭፍራ ሠራ:: በዚህ ጊዜ በእግዚአብሔር ቁጣ ሠራዊቱ መቅሰፍት ይፈጀው ጀመር:: በዚህም ሁኔታ ንጉሡ ተደናግጦ ምን መደረግ እንዳለበት የሀገሪቱ ተወላጆች ማለት የሰማርያን ሰዎች ቢጠይቃቸው በዚህ ሀገር ያዕቆብ አባታችን እግዚአብሔር አምላካችን የማይል ሰው ሊኖር አይችልም ብለው ነገሩት:: ከዚህ በኋላ ምናሴ የሚባል ካህነ ሰማርያ ወይም የሰማርያ ካህን አስተምራቸው ብሎ ሰደደላቸው:: እሱም አስተምሮ ኦሪትን ጻፈላቸው:: ይኼውም ኦሪተ ሳምራውያን ወይም የሳምራውያን ኦሪት ተባለ::

4ኛ. *ኦሪተ አይሁድ ይባላል::* ምክንያቱም አይሁድ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ገና ሥጋን ከመልበሱ ማለት ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ነስቶ ከመዋሃዱ አስቀድሞ ሥጋን ለበሰ:: ጊዜው ሳይደርስ ጊዜው ደረሰ እንዴት ትላለህ? ብለው በቅዱስ እስጢፋኖስ ተነሱበት:: እስጢፋኖስም ሰባኤ ትውልድ ዘሄኖክ፣ ሰባኤ ትውልድ ዘኤርምያስ አምጥቶ ሰፍሮ ቆጥሮ ዘመኑን ከእነ ትውልዱ አስማምቶ ከመጻሕፍተ ነቢያት ምስክር ሰጥቶ ቢረታቸው በድንጊያ ወግረው ገደሉት::

ከዚህ በኋላ ትንቢተ ሥጋዌን ለወጡት ከትውልዱም አንድን /አንዱን/ ዓመተ ቃይናንን ለወጡት ኦሪተ ሌዋውያኑንም እንደዚሁ ለወጡት:: ዘመኑንም አዳም ሴትን በ230 ዓመተ ዓለም ወለደው ያለውን በ130 ብለው ቆጠሩት:: ሴት ሄኖክን በ205 ወለደው ያለውን በ105 ብለው ቆጠሩት:: በዚህ ዓይነት መልኩ እስከ አብርሃም ድረስ አንድ ሺህ 500 ዘመን ቀንሰው ቆጠሩ:: በዚህ ኦሪተ ሌዋውያ ኦሪተ ሊቃውንትና ኦሪተ ሳምራውያን ጠፉ:: ኦሪተ አይሁድ ብቻ ቀረ:: ከዚህ በኋላ በሰሎሞን ጊዜ ሌዋውያን በ1ሺህ ዓመተ ዓለም ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ መጻሕፍቶቻቸውን ይዘው ስለመጡ ወይም ስለገቡ ኢትዮጵያ ኦሪተ ሌዋውያንን ስትቀበል ሌሎች ሀገራት ኦሪተ አይሁድን ተቀበሉ:: እንግዲህ በዚህ ዓይነት ምክንያት ነው የኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠርና የሌሎች ሀገራት የዘመን አቆጣጠር ሊለያይ የቻለው:: እንግዲህ ከረጅሙ ባጭሩ ከብዙ በጥቂቱ የዘመን አቆጣጠር ልዩነቱ ይህን ይመስላል:: ❖❖❖

www.ethiopianorthodox.org